# በደስታ መጽናት!

**መመሪያ፦** ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።
**ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦** ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ሲላስ፣ ሴት አገልጋይ፣ የሴቷ አገልጋይ ጌቶች እና የእስር ቤት ጠባቂ
**ታሪኩ በአጭሩ፦** ጳውሎስና ሲላስ ሲሰብኩ ተይዘው ታሰሩ፤ ይሁን እንጂ የምድር መናወጥ ተከስቶ ነፃ ወጡ።

## 1 ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—የሐዋርያት ሥራ 16:16-40ን አንብብ።

ከታች የተጠቀሱት ሰዎች ፊት ላይ ምን “ይታይሃል”?
የአገልጋይዋ ጌቶች ፊት (*ከቁጥር 19-22ን እንደገና አንብብ።*)

---

ጳውሎስ እና ሲላስ በእስር ቤት ሳሉ (*ቁጥር 25ን እንደገና አንብብ።*)

---

“ከባድ የምድር ነውጥ” በተከሰተበት ወቅት ምን ዓይነት ሁኔታ እንደነበረና ድምፁ ምን ይመስል እንደነበር ለመግለጽ ሞክር። (*ቁጥር 26, 27ን እንደገና አንብብ።*)

---

ሐዋርያው ጳውሎስ ከቁጥር 28-31 ላይ ያለውን ሐሳብ ለእስር ቤቱ ጠባቂ ሲናገር ምን ዓይነት የድምፅ ቃና የነበረው ይመስልሃል?

---

## 2 ጥልቅ ምርምር አድርግ።

ይህ የምድር መናወጥ በአጋጣሚ የተከሰተ ተፈጥሯዊ ክስተት ነው? እንደዚህ ብለህ የመለስከው ለምንድን ነው? (ፍንጭ፦ የሐዋርያት ሥራ 4:31ን፣ 5:19ን እና 12:7ን አንብብ።)

---

---

የእስር ቤቱ ጠባቂ፣ ጳውሎስና ሲላስ ደግነት ሲያሳዩት የተገረመው ለምን ሊሆን ይችላል? (*የሐዋርያት ሥራ 16:23, 24ን እንደገና አንብብ።*)

---

---

---

ጳውሎስና ሲላስ የደረሰባቸው ስደት ለሌሎች ለመስበክ አጋጣሚ የፈጠረላቸው እንዴት ነው? (ፍንጭ፦ *ቁጥር 25ን እና 33ን እንደገና አንብብ።*)

---

---

---



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 3 ከዚህ ታሪክ ያገኘኸውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ።

ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦

መከራ ሲያጋጥም መጽናት ስለሚቻልበት መንገድ

________________________________________

________________________________________

ጽናት ስለሚያስገኛቸው ጥቅሞች (ያዕቆብ 1:2-4ን አንብብ።)

________________________________________

________________________________________

## 4 ራስህን ጠይቅ።

ጽናት የሚያስፈልገኝ በተለይ በየትኞቹ ሁኔታዎች ውስጥ ነው?

________________________________________

________________________________________

ጽናት የሚጠይቅ ሁኔታ በሚያጋጥመኝ ወቅት፣ ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት ረገድ ጳውሎስን መምሰል የምችለው እንዴት ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ከዚህ ታሪክ የማገኘው ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆነው ትምህርት የትኛው ነው? ለምን?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**ተጨማሪ ሐሳብ፦** የእስር ቤቱ ጠባቂ እንደሆንክ አድርገህ አስብ። የተፈጠረውን ሁኔታ በእሱ ቦታ ሆነህ ለመጻፍ ሞክር። ጠባቂው፣ ጳውሎስንና ሲላስን ሲያስራቸው፣ የምድር መናወጡን ሲመለከት በኋላ ላይ ደግሞ ከቤተሰቡ ጋር ሲጠመቅ የተሰማውን ስሜት ግለጽ።



JW.ORG™
ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ አውርደህ ማተም ትችላለህ



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania